# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

## የመኖ ምርት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 995/2016

መጋቢት/2016 ዓ/ም

**ማውጫ**

መግቢያ ............................................................

ክፍል አንድ ............................................................3

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ............................................................3

1. አጭር ርዕስ ............................................................3

2. ትርጓሜ ............................................................3

3. የተፈጻሚነት ወሰን ............................................................4

**ክፍል ሁለት** ............................................................5

**የመኖ ምርት ስለመመዝገብ** ............................................................5

**4. ስለምዝገባ፤** ............................................................5

**5. ማመልከቻ ስለማቅረብና የአመዘጋገብ ሂደት** ............................................................6

6. ስለ ምዝገባ ለውጥ ............................................................6

7. ስለ ዳግም ምዝገባ ............................................................6

**ክፍል ሦስት** ............................................................7

**የመኖ ምርት ለማስመዝገብ መቅረብ የሚገባቸው ሰነዶች** ............................................................7

**8. ሕጋዊ ሰነዶች** ............................................................7

9. የመኖ ምርት አጠቃላይ መግለጫ ሰነድ ............................................................7

አመልካቹ ስለ መኖ ምርቱ- ............................................................7

10. የመኖ ምርት አመራረት ሂደት የሚያሳይ ሰነድ ............................................................8

11. የመኖ ምርት ጥራት ቁጥጥር መግለጫ ሰነድ ............................................................8

**12. ስለ መኖ ምርት ማሸጊያ** ............................................................8

**13. ስለ መኖ ምርት ገላጭ ጽሁፍ** ............................................................8

**14. ስለ መኖ ምርት ደህንነት ሰነድ** ............................................................9

**ክፍል አራት** ............................................................10

አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ............................................................10

**15. የመኖ ምርት ምዝገባን ስለ መሰረዝ** ............................................................10

16. ስለ አገልግሎት ክፍያ ............................................................10

17. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች ............................................................10

18. መመሪያው የሚፀናበትጊዜ ............................................................10

**ዕዝሎች** ............................................................11

## መመሪያ ቁጥር 995/2016
## የመኖ ምርት ምዝገባ መመሪያ

ለእንስሳት አርቢው ህብረተሰብ የሚቀርብ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ በመኖ ምዝገባና ፈቃድ ላይ ያተኮረ ጠንካራ እና ውጤታማ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በሀገራችን የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ የተቀነባበረ መኖ ፤የመኖ ንጥረ ነገር እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ለእንስሳት መኖነትና ለመኖ ግብዓትነት ከመዋላቸው በፊት ምንጫቸውን አውቆ፤ ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን በማረጋገጥ የገበያ ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት፣ ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመኖ ምርት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር995/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. **"የተቀነባበረ መኖ"** ማለት ቢያንስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመኖ ግብዓቶችን በማደባለቅ የሚዘጋጅ የእንስሳት ምግብ ሲሆን ማሟያ መኖንም ያካትታል፣
2. **"ማሟያ መኖ"** ማለት ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብ የንጥረ-ምግብ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል በጠጣር፣ በዱቄት፣ ፈሳሽ ሁኔታ የሚዘጋጅ ሆኖ መድኃኒት የተጨመረበትን፣ የመድኃኒትነት ይዘት ያላቸዉን እና ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት ታስቦ የሚዘጋጁትን አያካትትም::
3. **"የመኖ ግብዓት"** ማለት የመኖ ጥሬ ዕቃ እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የሚያካትት ነው፡ ፡
4. **"የመኖ ጥሬ ዕቃ"** ማለት የተቀነባበረ መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል ማንኛውም ከዕጽዋት ወይም ከእንስሳት የሚገኝ ምርት ወይም ተረፈምርት ወይም በሳይንሳዊ ዘዴ የተፈበረከ ግብዓትን ያካትታል፣
5. **"የመኖ ምርት"** ማለት የtቀነባበረ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ፣ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር እና ማሟያ መኖን የሚያካትት ነው፤
6. **"ዘረመሉ የተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው የመኖ ግብዓት"** ማለት በዘመኑ የዕፅዋትና እንስሳት ርቢ ምህንድስና፣ በሰው ሠራሽ ዘዴ ከሌላ ሕያው የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረ መል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር የተጨመረበት የዘረ መሎች ይዘት፣ አቀማመጥና ባህርይ የተለወጠበት ሕያው የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤት ነዉ፤
7. **"ከአመንዣጊ እንስሳት የተገኘ የመኖ ግብዓት"** ማለት ከሚያመሰኩ እንስሳት የተገኘ፣ የተፈጨ ሥጋ፣ የተፈጨ አጥንት፣ ደም፣ አንጎል፣ አንጀት እና ሌሎችንም የቁራ ተረፈ ምርቶችን የሚያካትት ነዉ፤
8. **"የመኖ ፈቃድ ሰጪ አካል"** ማለት በባለሥልጣኑ የመኖ ሬጉላቶሪ ወይም ዉክልና የተሰጠዉና ለተግባሩም አግባብነት ያለዉ አካል ነዉ፤
9. **"የመኖ ጥሬ ዕቃ ደረጃዎች"** ማለት በሀገሪቱ የደረጃዎች አጽዳቂ ካዉንስል የፀደቀ የምርት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ሰነድ ነዉ፤
10. **"የጤና ምስክር ወረቀት"** ማለት አንድ የመኖ ምርት ጤናማ ስለመሆኑ እና በተመጋቢው እንስሳ ወይም የእንስሳዉን ምርት ዉጤት በሚመገበዉ አካል ላይ ጉዳት እንደማያስከትል የሚያረጋግጥ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሰነድ ነው፣
11. **"የምርመራ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት የመኖ ምርት ጥራት እና ደህንነትን የሚገልጽ በአምራች ድርጅቱ ላቦራቶሪ ወይም ተቀባይነት ካለዉ ሶስተኛ አካል ላቦራቶሪ የተሰጠ የምርመራ ዉጤት የሚያሳይ ሰነድ ነዉ::

12. **“ምዝገባ”** ማለት የመኖ ምርት ለገበያ ከመቅረቡ በፊት እንደ ምርቱ አይነትና ባህሪ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የሚመዘገብበት ሂደት ነው፤
13. **“አስመዝጋቢ”** ማለት የመኖ ምርት አምራች ወይም ወኪል ነው፣
14. **“የምርት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት”** ማለት ለምዝገባ የቀረበው የመኖ ምርት አምራች ድርጅት ተግባራዊ የሚያደርገው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እውቅና የተሰጠው የመልካም አመራረት ትግበራ እና የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ወይም የምግብ ደህንነት አተገባበር ሥርዓት ነው፤
15. **“የሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት”** ማለት ለምዝገባ የቀረበው የመኖ ምርት የተቀመጠውን የጥራትና ደህንነት መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ እውቅና በተሰጣቸው ላቦራቶሪዎች ተመርምሮ ሲረጋገጥ የሚሰጥ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ነው፤
16. **“የምዝገባ የምስክር ወረቀት”** ማለት አስመዝጋቢው ለምዝገባ የቀረበው የመኖ ምርት በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ወይም የዓለም አቀፍ ደረጃ ሚሟላቱ ሲረጋገጥ የሚሰጥ የብቁነት ሰነድ ነው፤
17. **“ከፍተኛ ለውጥ”** ማለት በመኖ ምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ጉልህ ለውጥ ሊያሳድር የሚችል እንደ የማምረቻ ቦታ፣ የምርት ማሸጊያ አይነት፣ የምርት ቀመር፣ የአመራረት ሂደት፣ የምርት የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የምርት ጥራት መስፈርት፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ለውጥ ነው፣
18. **“አነስተኛ ለውጥ”** ማለት በመኖ ምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ የማያሳድር የምርት ተወካይ፣ የምርት አርማ፣ የምርት የንግድ ስም፣ የአምራች ድርጅት ስም፣ የምርት የተጣራ ክብደት ወይም ተመሳሳይ ለውጥ ነው፤
19. **“የመኖ ምርት ጥራት”** ማለት የእንስሳውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልግ የንጥረ ነገር ይዘትን ይመለከታል፤
20. **“ባለስልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ነው፤
21. በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው ለንግድ ዓላማ በሀገር ውስጥ ተመርቶ ክልል ተሻጋሪ በሆነ ወይም ከሀገር በሚወጣ ወይም ከውጭ ሀገር በሚገባ የመኖ ምርት ላይ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የመኖ ምርት ስለመመዝገብ

**4. ስለምዝገባ፤**

1. ***ማንኛውም የመኖ ምርት ፡-***

   *ሀ. ለንግድ ዓላማ ከመዋሉ በፊት በባለስልጣኑ መመዝገብ አለበት፤*

   *ለ. በባለስልጣኑ ለመመዝገብ በሀገር አቀፍ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጣና የጸደቀ የጥራትና ደህንነት ደረጃን ማሟላት ይኖርበታል፤*

2. *ማንኛውም ሰዉ **የመኖ ምርት** ለማስመዝገብ በቅድሚያ በመኖ ንግድ ለመሰማራት በባለስልጣኑ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፤*

3. *ዘረመሉ የተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው ወይም የዕድገት ማነቃቂያ ሆርሞን ይዘት ያለው ወይም መድሓኒት የተጨመረበት ወይም የመድሓኒትነት ይዘት ያለዉ የመኖ ግብዓት በሀገር ዉስጥ እንዲመረት ወይም ወደ ሀገር ዉስጥ እንዲገባ ሊመዘገብ አይችልም፤*

4. *የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* (1) *ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥራትና ደህንነትን በማረጋገጥ ብቻ ምዝገባ ሳያስፈልግ **የመኖ ምርት** ወደ ሀገር ውስጥ ሊገባ የሚችለው ፡-*

   *ሀ. ለሳይንሳዊ ምርምር ጠቀሜታ የሚዉል **የመኖ ምርት** ፤*

   *ለ. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች የቤት እንስሳት ፍጆታ የሚዉል የተቀነባበረ መኖ፤*

   *ሐ. በድርቅ፣ በጎርፍ፣ የመሬት ነዉጥና በመሳሰሉ አስገዳጅ ሁኔታዎች ወቅት ለደራሽ ዕርዳታ የሚውል **የመኖ ምርት***

   *መ. ግለሰቦች ለግል የቤት እንስሳት ፍጆታ ከራሳቸው ጋር ለሚያጓጉዟቸው እስከ* <u>10</u> *ኪ.ግ. ብቻ የሚሆን የተቀነባበረ መኖ።*

5. **ማመልከቻ ስለማቅረብና የአመዘጋገብ ሂደት**

1. ማንኛውም ሰው ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን **የመኖ ምርት** ለማስመዝገብ፣ በዚህ መመሪያ (በዕዝል 1) የተያያዘውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት፣ እና በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ ስምንት እስከ አስራ አራት የተጠቀሱትን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ አለበት፤
2. ማንኛውም አመልካች በሀገር ውስጥ የተመረቱ **የመኖ ምርት** ለማስመዝገብ፤ በዚህ መመሪያ በዕዝል 2 የተያያዘውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት፣ እና በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ ስምንት እስከ አስራ አራት የተጠቀሱትን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ አለበት፤
3. የሚቀርቡ የምዝገባ ማመልከቻዎች እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል የሚገመገሙ ይሆናል፤
4. ማንኛውም ሰዉ **የመኖ ምርት** ለማስመዝገብ አመልክቶ ከባለስልጣኑ ያልተሟላ ሰነድ ወይም ማብራሪያ በጽሁፍ እንዲያቀርብ እስከ ሶስት ጊዜ ተጠይቆ ተገቢውን ምላሽ በጽሁፍና በሰነድ የማይሰጥ ከሆነ በድጋሚ እንደ አዲስ ማመልከት አለበት፣
5. ባለስልጣኑ ለምዝገባ የሚቀርብ **የመኖ ምርት** ስምና ገላጭ ጽሁፍ ሰነድ እና ማስረጃ ሀገራዊ ወይም አለም አቀፋዊ ደረጃን መሰረት አድርጎ በማረጋገጥ የሚመዘግብ ይሆናል።
6. ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች መሟላታቸውንና የመኖ ምርቱ ናሙና በላብራቶሪ ተመርምሮ ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ ለአራት ዓመት የሚያገለግል የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

6. **ሰለ ምዝገባ ለውጥ**

1. ማንኛውም አስመዝጋቢ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ከወሰደ በኋላ **ከመኖ ምርቱ** ጋር ተያያዥነት ያለው ከፍተኛ ወይም አነስተኛ ለውጥ ሲኖር ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በማሳወቅ የለውጥ ምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፤
2. በመኖ ምርቱ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሲኖር አስመዝጋው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10፣11፣12 የተጠቀሱትን ሰነዶች እና የመኖ ምርት ናሙና አብሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤
3. በመኖ ምርት ላይ አነስተኛ ለውጥ ሲኖር አስመዝጋቢው ለባሥልጣኑ ይህንን በጽሁፍ በማሳወቅ የምዝገባ ለውጥ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

7. **ሰለ ዳግም ምዝገባ**

1. ማንኛውም የተመዘገበ ምርት በምርቱ ይዘትና ማሸጊያ ላይ ከፍተኛ ወይም አነስተኛ ለውጥ ካልተደረገበት በስተቀር ለአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር ለሚገባ ምርት በየአራት ዓመቱ ዳግም መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣
2. የከፍተኛ ለውጥ ምዝገባ የተደረገበት የመኖ ምርት ለዳግም ምዝገባ የተቀመጠው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የለውጥ ምዝገባ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤
3. አስመዝጋቢው በዚህ መመሪያ በዕዝል 1 እና 2 ለውጭ ሀገር እና ለሀገር ውስጥ አምራች እንደቅደም ተከተሉ የተያያዘውን የዳግም ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አስመዝጋቢው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5፣6፣7፣8፣11፣ አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 11 የተጠቀሱትን ሰነዶች ከማመልከቻ ቅጹ ጋር ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
5. አስመዝጋቢው የመኖ ምርቱ የአመራረት ሂደት፣ ማሸጊያ እና ገላጭ ጽሁፍ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳልተደረገ እና በመጀመሪያ ምዝገባ ወቅት ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በጽሁፍ ማረጋገጥ አለበት፤
6. ለዳግም ምዝገባ ከሰነዶች በተጨማሪ የመኖ ምርት ናሙና መቅረብ አለበት፤

## ክፍል ሦስት

## የመኖ ምርት ለማስመዝገብ መቅረብ የሚገባቸው ሰነዶች

### 8. ሕጋዊ ሰነዶች

ማንኛውም አስመዝጋቢ በምዝገባ ወቅት የሚከተሉትን ሕጋዊ ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

1. ማንኛዉም ሰዉ በውጭ ሀገር ተመርቶ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የመኖ ምርትን ለማስመዝገብ ከአምራች ድርጅቱ ጋር ህጋዊ የስምምነት ውል ያደረገበትን ሰነድ ፤
2. የመኖ ምርቱ ከሶስተኛ ወገን አምራች ጋር በሚደረግ ውል መሰረት የተመረተ ከሆነ በአምራቹና በ አስመራች መካከል የተደረገ ሕጋዊ ስምምነት ከሚገልጸው ሰነድ በተጨማሪም በአስመራቹና ሀገር ውስጥ ካለ አስመጪ ወይም ተወካይ መካከል የተደረገ ህጋዊ ስምምነት ፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተጠቀሰው የስምምነት ውል ውስጥ ማናቸውም በመኖ ምርቱ ምክንያት የሚመጡ የእንስሳት ጤና እክሎች ሲኖሩ፣ የምርቱ ጥራትና ደህንነት በመጓደሉ ምክንያት ባለስልጣኑ የመኖ ምርቱ ከገበያ እንዲሰበሰብ በሚያዝበት ወቅት ሰብስቦ ወደ መጣበት ሀገር የመመለስ ሀላፊነት የአምራቹና የአስመጪው የጋራ ኃላፊነት እንደሆነ በግልፅ መጠቀስ ይኖርበታል፤
4. የአምራች ድርጅቱ የምርት ጥራት ቅሬታ አያያዝና እክል ካለ ምርት ከገበያ የሚሰበሰብበትና ወደ መጣበት ሀገር የሚመለስበት የአሰራር ስርዓትን የሚያሳይ ሰነድ ፤
5. ለአምራች ድርጅቱ በላኪው ሀገር አግባብ ባለው ፍቃድ ሰጭ አካል የተሰጠ የማምረት ፈቃድ፣
6. ለአምራች ድርጅቱ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የመልካም አመራረት ትግበራ ወይም የማምረት ምስክር ወረቀት፣
7. የመኖ ምርቱ ዘረመሉ ከተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው ግብዓት ነፃ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣
8. የእንስሳት ውጤቶች እና ተረፈ ምርቶች እንደ መኖ ምርት ጥሬ ዕቃነት የሚውል ከሆነ ከእብድ ላም በሽታ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ነጻ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፤
9. የመኖ ምርቱ በላኪው ሀገር በገበያ ላይ እየዋለ ስለ መሆኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣
10. እንደ አስፈላጊነቱ አምራች ድርጅቱ ተግባራዊ ያደረገው እውቅና ባለው ተቋም የተሰጠ የምግብ ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ምስክር ወረቀት ወይም የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
11. የአምራች ድርጅቱ አጠቃለይ መግለጫ፤
12. የመኖ ምርቱ ገላጭ ጽሁፍ ናሙና ፤
13. የሀገር ውስጥ አምራች ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ስለ ምርት ከገበያ ስለመሰብሰብ በተመለከተ፣ 6፣ 7፣ 10፣ 11 እና 12 ከተጠቀሱት ውጭ ያሉትን ሰነዶች እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡

### 9. የመኖ ምርት አጠቃላይ መግለጫ ሰነድ

አመልካቹ ስለ መኖ ምርቱ፡-

1. አጠቃላይ አካላዊና ኬሚካላዊ ባህሪ፣
2. ንጥረ ነገር ይዘት፣
3. ለምን ተግባርና ዓላማ እንደሚውል፣
4. የአጠቃቀም መመሪያ፣

9. ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎችና የአያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አከመቻቸት ሁኔታ በዝርዝር የሚገልጽ ሰነድ ማቅረብ አለበት።

10. የመኖ ምርት አመራረት ሂደት የሚያሳይ ሰነድ

የመኖ ምርቱን ለማስመዝገብ የአመራረት ሂደቱን የሚያሳዩ የሚከተሉት ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡-

1. የመኖ ምርቱን ለማምረት እንደ ግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች ዝርዝር፣ የጥራትና ደህንነት ሰነድ፣ እና ምንጫቸውን የሚገልጽ ሰነድ፤
2. የመኖ ምርቱን የአመራረት ጥንቅር ወይም ቀመር የሚያሳይ ሰነድ፤
3. የመኖ ምርቱን የአመራረት ሂደት ቅደም ተከተል የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ፣
4. የእያንዳንዱን የአመራረት ሂደት ትግበራ ዝርዝር መግለጫ፣
5. በእያንዳንዱ የመኖ ምርት ሂደት የሚከናወን የጥራትና ደህንነት የቁጥጥር ስራዎች የሚያሳያ ሰነድ፣
6. ቢያንስ የአንድ ዙር የምርት አመራረት መዝገብ ።

11. የመኖ ምርት ጥራት ቁጥጥር መግለጫ ሰነድ

የመኖ ምርትን ለማስመዝገብ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር የሚደረግበትን ስርዓት የሚያሳይ የሚከተሉት ሰነዶች በአመልካቹ መቅረብ አለባቸው፡-

1. የመኖ ምርቱ የጥራትና ደህንነት መስፈረት ፣
2. የምርመራ ዘዴ እና ቢያንስ የሦስት የተለያየ ባች የምርመራ ውጤት ምስክር ወረቀት፣
3. የምርመራ ዘዴው ትክክለኛነት ማረጋገጫ ሰነድ፣
4. የምርቱ መጠቀሚያ ጊዜ የተወሰነበት የእርጋታ ጥናት ሰነድ መያያዝ ሲኖርበት፣ የጥናት ሰነዱ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ሁኔታ ያገናዘበ መሆን አለበት።

## 12. ስለ መኖ ምርት ማሸጊያ

1. የመኖ ምርት ማሸጊያው ተፈጥሮአዊ ይዘትና የተሰራበት ጥሬ ዕቃ በዝርዝር መገለጽ አለበት፤
2. ማሸጊያው የመኖ ምርቱን ለማሸግ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ወይም የሚያሳይ ሰነድ መቅረብ አለበት፣
3. ማሸጊያው የመኖ ምርቱን የማይበክል፣ የተለያየ የአየር ጸባይን መቋቋም የሚችል እና ምርቱን ከብክለት የሚከላከል መሆን አለበት፣
4. የማሸጊያው የጥራት ቁጥጥር መስፈርትና የጥራት ምርመራ ዘዴው አብሮ መቅረብ አለበት።

## 13. ስለ መኖ ምርት ገላጭ ጽሁፍ

1. ማንኛውም የመኖ ምርት በግልጽ የተፃፈና የሚነበብ፣ የማይለቅ፣ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ ገላጭ ጽሁፍ ሊኖረው ይገባል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ገላጭ ጽሁፍ በመኖ ምርቱ ማሸጊያ ወይም ከመኖ ምርቱ ማሸጊያ ጋር አብሮ ተሰፍቶ በሚመጣ በቀላሉ በማይበላሽ ነገር ላይ የተጻፈ መሆን አለበት፣
3. ማንኛውም አስመዝጋቢ ድርጅት በምዝገባ ወቅት የመኖ ምርት ገላጭ ጽሁፍ ናሙና ማቅረብ አለበት፤
4. ማንኛውም የተለጠፈ፣ የታሰረ፣ ስርዝ ድልዝ ያለበትና የማይነበብ ገላጭ ጽሁፍ ተቀባይነት አይኖረውም፣
5. ተጠቃሚውን ሊያሳስቱ የሚችሉ ቃላትና ምስሎች በገላጭ ጽሁፉ ውስጥ መካተት የለባቸውም፣
6. የመኖ ምርቱ በአገር ውሰጥ የሚመረት ከሆነ እና አስገዳጅ ደረጃ የወጣለት ከሆነ የብሄራዊ

አስገዳጅ ደረጃ ምልክት መለጠፍ ይኖርበታል፤

7. የመኖ ምርቱ ገላጭ ጽሁፍ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፤

    ሀ. የአምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤

    ለ. የምርቱ የንግድ ስም፤

    ሐ. የምርቱ ስም፤

    መ. የተመረተበት ቀንና ዓመት ምህረት፣

    ሠ. የምርት መለያ ቁጥር፣

    ረ. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜ፣

    ሰ. የመኖ ምርቱ የንጥረ ነገር ይዘት፣

    ሸ. በመኖ ምርቱ ዉስጥ የተካተቱት ጥሬ ዕቃዎች ዝርዝር ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸዉ፤

    ቀ. የተጣራ ክብደት፣

    በ. የመኖ ምርቱ ለየትኛዉ የእንስሳት ዓይነት፣ የዕድሜ ክልል፣ የምርት ዓይነትና ደረጃ እንደተዘጋጀ የሚገልጽ መረጃ በግልጽ መስፈር አለበት፤

    ተ. የመኖ ምርቱ ስለሚጓጓዝበትና ስለሚከማችበት ሁኔታና መደረግ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ ወይም ማስገንዘቢያ ወይም ማስጠንቀቂያ መስፈር ይገባዋል፡፡

## 14. ስለ መኖ ምርት ደህንነት ሰነድ

1. በምዝገባ ወቅት የመኖ ምርቱ በተጠቃሚው እንስሳ፣ ሰው፣ እና አካባቢ ላይ ምንም ዓይነት የጤና ችግር ሊያስከትል ከሚችል ቁሳዊ፣ ስነሕይወታዊ እና ኬሚካላዊ ጠንቆች ነፃ ስለመሆኑ የሚገጽ ሰነድ መቅረብ አለበት፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ሰነድ በአምራች ድርጅቱ የተሰራ የምርት ደህንነት ጥናት ሪፖርት ወይም በሌላ አካል የተሰራና በታወቀ ሳይንሳዊ ጆርናል ላይ የታተመ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 15. የመኖ ምርት ምዝገባን ስለ መሰረዝ

ማንኛውም የተመዘገበ የመኖ ምርት ከሚከተሉት ጥፋቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ የምዝገባ ወረቀቱን ሊሰረዝ ይችላል፡-

1) ማንኛውም የመኖ ምርት በየአራት ዓመቱ ዳግም ካልተመዘገበ፤
2) በተመዘገበው የመኖ ምርት ላይ የጥራትና ደህንት ጉድለት ሲኖር፤

### 16. ስለ አገልግሎት ክፍያ

የመኖ ምርትን ለማስመዝገብ፣ ለለውጥ ምዝገባ እና ዳግም ምዝገባ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት በሚወሰነው የአግልግሎት ክፍያ ተመን መሰረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

### 17. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣም ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 18. መመሪያው የሚፀናበትጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አምባሳደር ድሪባ ኩማ
የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

**ዕዝሎች**

እዝል 1፡ በውጭ ሀገር ተመርቶ ወደ ሀገር የሚገባ ምርት የምዝገባ መጠየቂያ ቅጽ

| **ተ.ቁ** | **ርእስ** | **በአመልካች የሚሞላ** |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |
| 1.1. | ሥም | |
| 1.2 | ሙሉ አድራሻ | ክልል ………………………፣ ዞን/ክ/ከተማ / ወረዳ/ቀበሌ<br>የቤት ቁጥር ……………………<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ<br>…………………………………………………………………<br>………………… |
| 2. | **የማመልከቻው አይነት** | አዲስ ☐ ዳ ☐ የም ☐<br>ለውጥ |
| 3. | **የምርት አስመጪ/ተወካይ** (importer/agent) | |
| | 3.1. የድርጅቱ ሥም | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ………………………፣ ዞን/ክ/ከተማ / ወረዳ/ቀበሌ<br>የቤት ቁጥር ……………………<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ<br>…………………………………………………………………<br>………………… |
| | 3.3. የድርጅቱ ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምርቱ አምራች ድርጅት** | |
| | 4.1. ሥም | |
| | 4.2. ሙሉ አድራሻ | ሀገር--------- ከተማ-------------የመንገድ ቁጥር------ ስልክ ቁጥር-----------ፋክስ የፖ.ሳ.ቁ…………………………………… ኢ-ሜይል ……………………………… ድህረ ገፅ፣…………………………………. |
| | 4.3. የአምራች ድርጅት ስም ወይም ተወካይ ሥም | |
| 5. | **የምርቱ መረጃ** | |
| | 5.1. የምርቱ ስም (የወል፣ የንግድ ስም) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣<br>ቀለም ሌሎች በዐይን የሚታዩ መስፈርቶች ወዘተ) | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ የክብደት መጠን | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ አይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 5.7. የምርቱ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን | |
| | 5.8. ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓት ዝርዝር | |
| | 5.9. ምርቱን ለማስመዝገብ መሟላት ያለባቸውን ሰነዶች በእንግሊዝኛ በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፣ | |
| 6 | **የምርት ምዝገባና ፍቃድ ሁኔታ** | |
| | 6.1. ምርቱ የተመዘገበበትና ፍቃድ ያገኘባቸው<br>ሀገራት | |
| | 6.2. ወደ ገበያ እንዳይቀርብ የታገደባቸውና<br>በጥራትና ደህንነት ጉድልት ከገበያ እንዲሰበሰቡ<br>የተደረገባቸው ሀገራት ስም ዝርዝር | |
| 7 | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን<br>እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለሁ።<br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br>ሥም: ______________________________<br>ፊርማ: ______________________________<br>በድርጅቱ ያለው ሃለፊነት: ________________________<br>ቀን: ______________________________<br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ____________________ | |
| 8 | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | |

| ተ.ቁ | ርእስ | | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|---|
| | ማመልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት | | |
| | ማመልክቸውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ | | |

እዝል 2: ለሀገር ውስጥ ምርት የምዝገባ መጠየቅያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |
| | 1.3.ሥም | |
| | 1.4.ሙሉ አድራሻ | ክልል ………………………..፣ ዞን/ክ/ከተማ /<br>ወረዳ/ቀበሌ የቤት ቁጥር …………………….<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ<br>…………………………………………………………………………………….……. |
| 2. | **የማሳወቂ ሁኔታ** | አዲስ ☐ ዳግ☐ ☐ጥ |
| 3. | **የአምራች ድርጅት** | |
| | 3.1 . ሥም፡ | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ………………………..፣ ዞን/ክ/ከተማ /<br>ወረዳ/ቀበሌ የቤት ቁጥር …………………….<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ<br>ይገለጽ ……………………………………………………………… |
| | 3.3. የአምራች ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምርት ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምርት ስም (የወል፣ የንምርት ስም (brand name)) ) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ቀለም በዓይን የሚታዩ መስፍረቶች ወዘተ) | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ ክብደት | |

| | | |
|---|---|---|
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ ዓይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 5.7 የምርቱ የንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን /በሰንጠረዥ የቀረበ / | |
| | 5.8 ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓት ዝርዝር | |
| 6 | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣<br>ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለው፡፡<br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br>*ሥም*: ______________________________<br>*ፊርማ*: ______________________________<br>በድርጅቱ ውስጥ ያሎት ሃለፊነት: ______________________________<br>*ቀን*: ______________________________<br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ______________________________ | |
| 7 | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማምልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት | | |
| | ማመልክቸውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ | | |

እዝል 3. ደረጃ የወጣላቸው የተቀነባረ የእንስሳት መኖ ዝርዝር

1. Compound feeds for pigs ( pig starter, grower, finisher, breeding snow, lactating snow, pregnant snow)
2. Compound chicken feed (layer)
3. Compound chicken feed (broiler)
4. Compound chicken feed (breeder)
5. Compound feed for lactating dairy cows
6. Compound feed for pregnant dairy cows
7. Compound feed for dairy heifers
8. Compound feed for fattening cattle
9. Compound feed for fattening sheep and goats

10. Compound feed for Ewes ( pregnant, lactating, and breeding ewes)
11. Compound feed for breeding rams
12. Compound feed for Does ( pregnant, lactating, and breeding ewes)
13. Compound feed for breeding Bucks
14. Compound feed for Tilapia
15. Mineral mixtures for supplementing compounded poultry feed
16. Mineral mixtures used to supplement small ruminant( sheep and Goats)
17. Mineral mixtures use to supplement cattle feed
18. Compound poultry and pigs feed supplements ( Meat meal and meat and bone meal)
19. Compound young cattle feed supplements (calf starter and calf growth)

## አዝል 4. ደረጃ የወጣላቸው የመኖ ጥሬ ዕቃ ዝርዝር

1. Bone meal ES1034 -2019
2. SUNFLOWER CAKE ES1043-2019
3. SESAME CAKE ES 1044-2019
4. COTTONSEED CAKE ES 1037-2019
5. NIGER SEED CAKE ES1040-2019
6. RAPE SEED CAKE ES 1041-2019
7. SAFFLOWER CAKE ES 1042-2019
8. LINESEED CAKE ES 1039-2019
9. BREWERY BY PRODUCT ES 1047-2019
10. GROUNDNUT CAKE ES 1038-2019
11. FISH MEAL ES 1036-2019
12. BLOOD MEAL ES 1035-2019
13. SOYABEAN CAKE ES 1045-2019
14. WHEAT MILLING BY-PRODUCTS ES 1049-2019
15. MAIZE AND MAIZE BY-PRODUCTS ES 1048-2019

## አዝል 5. የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ምድብ (Categories of Feed Additives)

**1. Technological additives:-**

1.1 Preservatives
1.2 Antioxidants
1.3 Emulsifiers
1.4 Stabilizers
1.5 Thickeners
1.6 Gelling agents
1.7 Binders
1.8 Substances for the control of radionuclide contamination
1.9 Anti-caking agents
1.10 Acidity regulators
1.11 Silage additives
1.12 Denaturants

**2. Sensory additives**

2.1 colorants
2.2 flavoring compounds

**3. Nutritional additives**

3.1 Vitamins, pro vitamins, & chemically well-defined substances having similar effect
3.2 Compounds of trace elements
3.3 Amino acids, their salts and analogues
3.4 Urea and its derivatives

**4. Zoo technical additives**

4.1 Digestibility enhancers

4.2 Gulf flora stabilizers